# ETHIOPIAN CIVIL SERVICE UNIVERSITY
# የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

Quarterly Magazine
Oct-Dec 2024



## የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የጥናት የማማከር ውል ስምምነት ሰነድ ከአዲስ አበባ ሥራና ክህሎት ቢሮ ጋር ተፈራረመ



በኢሲሰዩ የራስ-ገዝነት ረቂቅ የሽግግር ሰነዶች ላይ ዉይይት ተካሄደ



የከተማ ማስፋፊያ ፕላን የህግ ማዕቀፍ አስፈላጊነት ላይ የምክክር ወርክሾፕ ተካሄደ

## ራዕይ

ፐብሊክ ሴክተሩን ከመገንባት አኳያ በ2022 በዘርፉ ከተሰማሩት ተቋማት መካከል የላቀ፣ በቴክኖሎጂ የዘመነና ተወዳዳሪ የአቅም መገንቢያ ተቋም መሆን

## ተልዕኮ

ፐብሊክ ሴክተሩ ውጤታማ የህዝብ አገልጋይ ሆኖ እንዲሰራ አቅሙን በስፔሻላይዝድ ትምህርት፣ በስልጠና፣ በማማከር፣ በጥናትና ምርምር እና በማህበረሰብ አገልግሎቶች በቀጣይነት መገንባት

## እሴቶች

ተገልጋይ ተኮር

ልቆ መገኘት

ተባብሮ መሥራት

ሁሌም መማር

ፈጠራን ማበረታታት

ዘለቄታዊ ውጤታማነት

ብዝሀነትን መቀበል

ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ

# Table of contents


የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ጥናት የማማከር ውል ስምምነት ሰነድ ከአዲስ አበባ ሥራና ክህሎት ቢሮ ጋር ተፈራረመ........1

በቁልፍ የውጤት አመላካቶች ላይ ማብራሪያ ተሰጠ........2

የከተማ ማስፋፊያ ፕላን የህግ ማዕቀፍ አስፈላጊነት ላይ የምክክር ወርክሾፕ ተካሄደ........3

ኢሲሰዩ በትምህርት ዘርፉ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን በተቀናጀ መልኩ ማሻሻል የሚያስችል ስምምነት ተፈረመ........4

የባህሪያዊ ብቃት ስልጠና ሞጁል ዝግጅት ተጀመረ........4

በኢሲሰዩ የራስ-ገዝነት ረቂቅ የሽግግር ሰነዶች ላይ ዉይይት ተካሄደ........5

የዓለም አቀፍ የኤች አይ ቪ/ኤድስ፣ የአካል ጉዳተኞች እና ጾታዊ ጥቃትን የመከላከል ቀን በኢሲሰዩ ተከበረ........9

ECSU held a Conference on Migratory Trends in the Horn of Africa........10

ECSU President and NSG Principal Holds Meeting on Bilateral Cooperation........13

An Online Event Holds at ECSU........14

ECSU Gives Orientation for New Entry Students........14

ECSU President Discusses with Cultural Affairs Officer at the US Embassy ........15

ECSU Holds a seminar on Necessity of Tax Reform for Ethiopia**........16**

International Bureau of Fiscal Documentation Delegates Visits ECSU........17

ECSU Holds a Seminar on different programs and Opportunities provided for scholars by US Government........18

SGS Organizes PhD Dissertation Defense Programs........20

# የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ጥናት የማማከር ውል ስምምነት ሰነድ ከአዲስ አበባ ሥራና ክህሎት ቢሮ ጋር ተፈራረመ

የአዲስ አበባ ሥራና ክህሎት ቢሮ የኢንተርፕራይዞችን የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር ገበያ ትስስር ውጤታማነትና ዘላቂነት ለማረጋገጥና ፀጋን ለመለየት የሚያስችል ጥናት የማማከር ውል ስምምነት ሰነድ ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ጋር ተፈራርሟል።



ኢንተርፕራይዞች የሚገጥማቸውን ችግር በጥናት በመለየት በጥናቱ ግኝት መሰረት አሰራርን በማሻሻል እና ለፖሊሲ ግብአት ከመጠቀም ባለፈ የመክሰም ምጣኔ በመቀነስ እና ዘላቂ የገበያ ትስስር በመፍጠር ሂደት የመፍትሄ ሃሳብ ለማቅረብ እንደሚያግዝ በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ሥራና ክህሎት ቢሮ ኃላፊ ክቡር አቶ ጥራቱ በየነ ተናግረዋል። የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ፕሬዘዳንት ፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ ዩኒቨርሲቲው ከዚህ ቀደም ከከተማ አስተዳደሩ የተለያዩ ተቋማት ጋር የተለያዩ ጥናትና





ምርምር ስራዎችን ማካሄዱን በማስታወስ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ጥናቱን ሰርቶ ለማስረከብ ከቢሮው ጋር በቅርበት እንደሚሰራ ተናግረዋል። በከተማዋ ከ24ሺ በላይ ኢንተርፕራይዞች እንደሚገኙ የተናገሩት በቢሮ ኃላፊ ማዕረግ የአዲስ አበባ ስራና ክህሎት ቢሮ የኢንተርፕራይዝና ቴክኖሎጂ ልማት ዘርፍ ኃላፊ አቶ መሀመድ ልጋኒ ጥናቱ ኢንተርፕራይዞች የሚገጥሟቸውን የሀገር ውስጥ የውጭ ሀገር የገበያ ትስስር ችግር በመፍታት እንደ ሀገር አርዓያ እንዲሆኑ ያስችላል ብለዋል።

ምንጭ፡- የአዲስ አበባ ሥራና ክህሎት ቢሮ

# በቁልፍ የውጤት አመላካቶች ላይ ማብራሪያ ተሰጠ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ (ኢሲሰዩ) ከኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር ጋር በተፈራረመው የዕቅድ አፈጻጸም ውል መለኪያ በሆኑት የቁልፍ ውጤት አመላካቾች (Key Performance Indicators/ KPI) ዙርያ ታህሳስ 25 ቀን 2017 ዓ.ም በህዳሴ አዳራሽ ገለጻ እና ማብራሪያ ተሰጠ።

ገለጻውን የሰጡት የኢሲሰዩ ፕሬዚደንት ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ ሲሆኑ በመርሀ- ግብሩ ላይም የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕሬዚደንቶች፣ ዲኖች ፣ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች እና ሥራ አስፈጻሚዎች ተሳትፈዋል።

ፕ/ር ፍቅሬ ለተሳታፊዎቹ ባደረጉት ገለጻም ከኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር ጋር ሁሉም የመንግስት ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንቶች አዲስ በተዘጋጀው የዕቅድ አፈጻጸም ውል የተፈራረሙ መሆናቸውን እና የስምምነት ውሉም ተቋማቱ የተጣለባቸውን ተልዕኮ አፈጻጸም ሊለኩ ይችላሉ ተብለው በተለዩ የቁልፍ የውጤት አመላካቾችን በዝርዝር ያካተተ መሆኑን ገልጸዋል። የስምምነት ውሉን መፈራረም አስፈላጊነትም ሲያብራሩ በሀገሪቱ የሚገኙ የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንደተቋም የተጣለባቸውን ኃላፊነትና ተልዕኮ በመወጣት ረገድ ከጊዜ ወደ ጊዜ በበርካታ ጉዳዮች የአፈጻጸም ክፍተት እየታየባቸው እና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እየተውጡ ባለመሆናቸው፣ ይህን እውነታ ለመለወጥና በቴክኖሎጂ የተደገፈ አሰራር እንዲኖር የተዘጋጀ መሆኑን አብራርተው የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲም በአምስት መሰረታዊ የትኩረት መስኮች ማለትም በመማር ማስተማር፣ በምርምር፣ በማህበረሰብ አገልግሎት፣ በአዓለምአቀፋዊነትና ግሎባላይዜሽን እንዲሁም በአመራርና አስተዳደር ላይ ያተኮሩ የየራሳቸው የሆነ መለኪያና መመዘኛ የተቀመጠላቸው ሰማንያ የውጤት አመላካቾችን በመለየት



ውል መፈራረሙን ገልጸዋል። እነዚህ ሰማንያ ርዕሰ ጉዳዮችም በአብዛኛው በዩኒቨርሲቲው ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ጋር የተያያዙ መሆናቸውና እንዴት እንተግብራቸው የሚለውን በጥልቀት በማየት በአግባቡ መተግበር እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል። ቁልፍ የውጤት አመላካቾችንም በዩኒቨርሲቲው ያለበትን ደረጃ የተተገበሩ፣ በመተግበር ላይ ያሉ እና ገና ያልተጀመሩ



ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ የኢሲሰዩ ፕሬዚደንት

በሚል በሶስት ደረጃ በመክፈል ያሳዩት ፕ/ር ፍቅሬ ከየዘርፍ ኃላፊዎች ጀምሮ ሁሉም በየደረጃው የእያንዳንዱን የውጤት አመላከች የያዘውን ጽንሰ-ሃሳብ በአግባቡ ተገንዝበ በቀሪዎቹ ስድስት ወራት ውስጥ መፈጸም እንደሚጠበቅበት እንዲሁም በተዘረጋው የክትትል እና የድጋፍ ስርዓት መሰረት በየደረጃው ሪፖርት የሚደረግ መሆኑን፣ የሚቀርበውም ሪፖርት እውነተኛ እና ተአማኒነት ያለው፣ በአግባቡ ተሰንዶ የሚቀርብ መሆን እንዳለበት ገልጸው እነዚህ የውጤት አመላካቾችን ለይቶ በተገቢው ደረጃ መፈጸም የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብም ሆነ የተቋሙን የወደፊት ዕጣ ፈንታ የሚወስን ዐብይ ጉዳይ በመሆኑ፣ ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾች ውል በተሰጡን ተግባራት ትኩረት አድርገን ስራዎችን እንድንሰራ ምቹ ሁኔታዎችን እንደሚፈጥሩ ገልጸዉ፤ በጥንቃቄና በትጋት ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ አስፋላጊ መሆኑን በአጽንኦት አሳስበዋል። በመርሀ ግብሩ ላይ የተገኙ የስራ ኃላፊዎችም በቀረበው ገለጻ ላይ ያላቸውን ጥያቄዎችና አስተያየቶች እንዲሁም ሊሟሉ ይገባሉ ያሏቸውን ግብዐቶች በዝርዝር ያቀረቡ ሲሆን ፕ/ር ፍቅሬ ለጥያቄዎቹ ማብራርያና ምላሽ ሰጥተዋል።

# የከተማ ማስፋፊያ ፕላን የህግ ማዕቀፍ አስፈላጊነት ላይ የምክክር ወርክሾፕ ተካሄደ

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ማስፋፊያ ፕላን የህግ ማዕቀፍ አስፈላጊነት በሚል ርዕስ የምክክር ወርክሾፕ ታህሳስ 22 ቀን 2017 ዓ.ም በህዳሴ አዳራሽ ተካሄደ። ወርክሾፑ የተካሄደውም በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ እና በከተማና መሰረተ-ልማት ሚኒስቴር ትብብር እንዲሁም በሲቲ አልያንስ የከተማ መስፋፋት ፕሮጀክት አማካይነት ሲሆን በወርክ ሾፑ ላይም ከፌደራል፣ ከክልል እና ከከተማ መስተዳደሮች የተወጣጡ አመራሮችና ባለሙያዎች ተሳትፈውበታል።

በወርክሾፑ መክፍቻ ላይ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ ባደረጉት የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክትየኢትዮጵያሲቪልሰርቪስዩኒቨርሲቲበመደበኛየትምህርት ፕሮግራሙ እና በሚሰጣቸው የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎች በከተማ



ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ የኢሲሰዩ ፕሬዚደንት

ልማት ዘርፍ በዓይነትም ሆነ በመጠን የሚያስፈልገውን የሰው አቅም በመገንባት ረገድ ለዓመታት መጠነ ሰፊ ስራዎችን እያከናወነ ከመሆኑም ባሻገር የከተማ መዋቅራዊና አከባቢያዊ ልማት ፕላን ዝግጅት ሥራዎችም በመስራትና በማማከር ጉልህ ሚናበመጫወትላይእንደሚገኝገልጸዋል።በሀገራችን ከተሞች ከደረሱበት የዕድገት ደረጃ አንጻርና ካለው ሁለንተናዊ የከተሞች ዕድገት ከማረጋገጥ አኳያ ብዙ ስራዎች መከናወን እደሚገባቸውም የገለጹት ፕ/ር ፍቅሬ አብዛኞቹ የሀገራትን ከተሞች በዘፈቀደ የጎንዮሽ እየተስፋፉ በመሄዳቸው የአገልግሎት ስርጭቱና የትራንስፖርት ሥርዓቱን አስቸጋሪ ከማድረጉም በላይ የመሰረተ-ልማት ዝርጋታውም በቀላሉ እንዳይሰለጥ በማድረግ ፣ የግብርና መሬትን በመሻማትና የተፈጥሮ ሚዛንን በማዛባት ቀላል የማይባል አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳረፈ መሆኑን አብራርተው ይህንን ሁኔታ ለመቀልበስ የከተሞችን የጎንዮሽ ዕድገት በመቆጣጠር የአግድሞሽና የሽቅብ ጥግግትን በማምጣት ሰብሰብ ያለ ከተማ መፍጠር የግድ መሆኑን ተናግረዋል። ከተማ ፕላን ስታንደርድ ሳይኖራቸው በየአቅጣጫው እየተመሰረቱ ላሉ ትንንሽና ታዳጊ የገጠር ከተሞችና መንደሮችም ከወዲሁ ትኩረት ተሰጥቷቸውና ባለቤት እንዲኖራቸው በማድረግ በከተማ ፕላን የሚመሩበት ሥርዓት መዘርጋትምጊዜየማይሰጠውዐብይጉዳይመሆኑንአመላክተዋል። ፕ/ር ፍቅሬ አክለውም የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ከከተማና መሰረተ-ልማት ሚኒስቴር እና ከሲቲ አልያንስ ጋር በመተባበር ያዘጋጀው ይህ ወርክ ሾፕ ዓላማው እስካሁን ድረስ ብዙም ትኩረት ያልተሰጠውን የከተማ ማስፋፊያ ፕላን ያለውን ፋይዳ በማስገንዘብ በሀገር አቀፍ ደረጃ ህጋዊ ማዕቀፍ እንዲኖረው ለማድረግ መሆኑን ጠቁመው የከተሞች ማስፋፊያ ፕላን የከተሞችን የወደፊት ዕጣ ፋንታ በመወሰን፣ ቀጣይነት ያለው ዕድገትን በማረጋገጥ እና በፈጣን የከተሞች መስፋፋት የሚስተዋሉ ውስብስብ ችግሮችን ለመፍታት ቁልፍ ሚና የሚጫወት እና የማዕዘን ድንጋይ በመሆኑ፣ ከተሞች ለትውልድ ምቹ የሆኑና የበለጸጉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ወጥ በሆነ የፖሊሲ ማዕቀፍ መመራት አማራጭ የሌለው፣ ልዩ ትኩረት የሚሻ መሆኑን በአጽንኦት አሳስበው ይህን ዐብይ ጉዳይ በመገንዘብ ወርክሾፑን ላዘጋጁት አካላትም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።





በውክሾፑ ላይ የከተማ ማስፋፊያ ፕላን የህግ ማዕቀፍ አስፈላጊነት ላይ የተዘጋጀ የመወያያ ሰነድ በዶ/ር ሂርጳ በረሶ የከተማ ልማትና ምህንድስና ኮሌጅ ም/ዲን አማካይነት የቀረበ ሲሆን በሰነዱ ላይም እስካሁን አሳሪ የሆነ የከተሞች መስፋፋት የህግ ማዕቀፍ አለመኖሩ ተመላክቶ፤ የህግ ማዕቀፉ አስፈላጊት ላይ ግን በሁሉም ዘንድ ተቀባይት ያለው መሆኑ ተገልጿል። የተዘጋጀው ሰነድም የተለያዩ ሀገሪቷ የምትመራባቸውን አዋጆችን፣ ፖሊሲዎችን፣ መመሪያዎችና ስትራቴጂዎችን በስፋትና በጥልቀት በመዳሰስ እንዲሁም የባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት የተዘጋጀ መሆኑንም ዶ/ር ሂርጳ ያቀረቡ ሲሆን ቤቱም በህግ ማዕቀፉ አስፈላጊነትና በተጨባጭ በከተሞች መስፋፋት ረገድ እየተስተዋሉ ያሉ ተግዳሮቾችን በማንሳት እና የመፍትኄ ሀሳቦችን በማቅረብ በስፋት ተወያይቶባቸዋል።

## ኢሲሰዩ በትምህርት ዘርፉ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን በተቀናጀ መልኩ ማሻሻል የሚያስችል ስምምነት ተፈራረመ።

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ዶ/ር ተመስገን ቡርቃ እና የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ በትምህርት ሚኒስትር በተዘጋጀዉ በቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾች / Key Performance Indicators ስምምነት ታህሳስ 16 ቀን 2017 ዓ.ም ተፈራረሙ።




ስምምነቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ 47 የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎችየቦርድሰብሳቢዎችናየዩኒቨርሲቲፕሬዝዳንቶች በተገኙበት የተከናወነ ሲሆን ስምምነቱም በዋናነት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሳይንሳዊና ዓለም አቀፋዊ መለኪያች ላይ ያተኮረእድገትእንዲኖራቸው፣የከፍተኛትምህርትተቋማትን ስራንበውጤትመምራትእንዲችሉ፣ብቃትያለውየሰውሃይል ለማፍራትናፋይዳቸውየጎላችግርፈቺየምርምርስራዎችላይ እንዲያተኩሩ ፣ በዘርፉ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን በተቀናጀ መልኩ እንዲፈቱ እና እንደተቋም የተጣለባቸዉን ሀላፊነት በጥራት እና በብቃት እንዲያከናዉኑ ያሚያስችል ነዉ።

## የባህሪያዊ ብቃት ስልጠና ሞጁል ዝግጅት ተጀመረ

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የባህሪያዊ ስልጠና ሞጁል ዝግጅት ፕሮጀክት ይፋዊ የማስጀመሪያ ፕሮግራም ታህሳስ 15 ቀን 2017 ዓ.ም በህዳሴ አዳራሽ ተካሄደ። የባህሪያዊ ብቃት ስልጠና ሞጁልም ከኢፌዴሪ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በተደረሰ የመግባቢያ ሰነድ መሰረት የሚዘጋጅ የመንግስት ሰራተኞችን ብቃት ለማሳደግ የሚዘጋጅ ሰነድ መሆኑም በመድረኩ ተገልጻል።

በፕሮግራሙ መክፈቻ ላይ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ፕ/ር ፍቅሬ ዳሳለኝ ባስተላለፉት መልዕክት በፌዴራል ሆነ በክልል እንዲሁም በከተማ መስተዳደሮች የሚገኙ አመራሮችና ባለሙያዎች የተጣለባቸውን ኃላፊነትና የስራ ድርሻ በአግባቡ እየፈጸሙ አለመሆናቸው እና የመንግስት አገልግሎት ዘርፉ



በመንግስት የተሰጠውን ተልዕኮ የመሸከም የብቃት ችግር እንዳለበት በጥናት የተረጋገጠ መሆኑን አስታዉሰው በተያዘው ታላቅ የለውጥ አቅጣጫ በየደረጃው ያለውን ክፍተት በምዘና በመለየት በስልጠናመሙላትአስፋላጊመሆኑእንደታመነበትገልጸዋል።ለዚህ የለውጥ አጀንዳም በተዘጋጀው ማዕቀፍ መሰረት የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የባህሪያዊ ብቃት የስልጠና ሞጁል አዘጋጅቶ ለስልጠና ዝግጁ የማድረግ ኃላፊነት የተሰጠው መሆኑን ፕ/ር ፍቅሬ ገልጸውለዚህዝግጅትየተመረጡአዘጋጆችእንደምሁርየሚያዘጋጁት ሞጁል በስፋቱም ሆነ በጥራቱ ጀረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ብሎም በሀገሪቱ ያሉ የመንግስት ሰራተኞችን አቅም በመገንባት ለሀገር እድገትን የሚያመጣ ሰነድ መሆኑን በአግባቡ በመውሰድ በታላቅ ሀገራዊ የኃላፊነትስሜት መዘጋጀት እንደሚገባው በአጽንኦት አሳስበዋል፡፡



ዶ/ር ደጉሰው ተሰማ የስልጠና ኢንስቲትዩት ምክትል ዲን በበኩላቸው የስልጠና ሞጁሉን አዘገጃጀት አስመልክቶ ባቀረቡት ገለጻ ለዝግጅቱ በብቃታቸውና በችሎታቸው የተመረጡ ሰላሳ ባለሙያዎች የተመረጡ መሆናቸውን ገልጸው የሚዘጋጀው ሞጁልም ሶስት የብቃትአሀዶችንማለትምሥነ-ምግባርናተምሳሌትነት፣አገልጋይነት እና ብዝሃነትና አካታችነት በሚሉ ማዕቀፎች እያንዳንቸው አስር በጠቅላላው ሰላሳ ሞጁሎች የሚዘጋጁ መሆናቸውን ገልጸዋል።

# በኢሲሰዩ የራስ-ገዝነት ረቂቅ የሽግግር ሰነዶች ላይ ዉይይት ተካሄደ

የኢትዮጲያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስትር በተቀመጠዉ አቅጣጫ መሰረት ወደ ራስ-ገዝነት በሚያደርገዉ ጉዞ ሁለተኛ ምዕራፍ ሂደት ላይ ደረሰ።

ዩኒቨርሲቲው ሁለተኛውን የራስ ገዝነት ምእራፍ ለማሳካት እና ወደ ትግበራ ለመግባት የሚያግዙ የተለያዩ ረቂቅ ሰነዶችን አዘጋጅቶ፣ በተዘጋጁት ረቂቅ ሰነዶች ላይ ተከታታይ የሆነ ግምገማዊ ወርክሾፖች ተካሂደዋል። በወርክሾፖቹ



ላይም በቀረቡት ረቂቅ ፖሊሲዎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች በተሳታፊዎቹ ዝርዝር ውይይት ተካሂዶባቸዋል። ህዳር 27፣ታህሳስ 4 እና ታህሳስ 11 ቀን 2017 ዓ/ም በህዳሴ አዳራሽ በተደረገው ውይይት ላይ የቀረቡት ረቂቅ ሰነዶች “የኢሲሰዩ የተማሪዎች ምልመላ፣ መረጣና ቅበላ ረቂቅ ፖሊሲ፣የኢሲሰዩ የስልጠና ጥራት ማስጠበቂያ ረቂቅ ፖሊሲ፣ የኢሲሰዩ የአካዳሚክ ሰራተኞች አፈጻጸም ምዘና ረቂቅ መመሪያ፣ የኢሲሰዩ የምርምር አስተዳደር ረቂቅ መመሪያ ፣ የኢሲሰዩ የምርምር በጀት ድጋፍ አስተዳደር ረቂቅ መመሪያ እና የኢሲሰዩ የተመራቂ ተማሪዎች ምርምር ማስተባበሪያና ድጋፍ ረቂቅ መመሪያ ” የሚሉት ናቸው። በወርክሾፑ ላይ የቀረቡት ሰነዶች ለውይይት እንዲመቹ ተደርገው በሶስት ዙር የተደራጁ ሲሆኑ ሁሉም ሰነዶች ዩኒቨርሲቲው በአገር አቀፍ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ልየታ መሰረት የምርምር ዩኒቨርሲቲ ተብለው ከተለዩት የሀገራችን አንጋፋ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል አንዱ መሆኑን እና ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስትር በተቀመጠዉ አቅጣጫ መሰረት በ2018 ዓ.ም ከጥገኝነት ምዕራፍ ተላቆ ወደ ከፊል ራስ-ገዝነት መሸጋገሩን ታሳቢ በማድረግ ልየታቀውን እና ሽግግሩን የተሳካ ለማድረግ መደላድል ሆነው የሚያገለግሉ ሰነዶች መሆናቸው ተመላክቷል። በሶስቱም ምእራፍ የውይይት መድረክ ላይ ተገኝተው የረቂቅ ሰነዶቹን ይዘት ላይ ማብራሪያ ሰጥተው ውይይቱን ያስጀመሩት የዩኒቨርስቲዉ ፕሬዚዳንት ፕ/ር ፍቅሬ ዳሳለኝ ሲሆኑ፣ በመግቢያው ላይ፣ በመላው አገሪቱ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች በአብዛኛው በለውጥ ሂደት ውስጥ እያለፉ መሆናቸውን አስታውሰው፣ “ከእነዚህ ለውጦች መካከል አንዱ፣ የዩኒቨርሲቲዎችን የመምራት እና የአስተዳደር ሥርዓትና ማዕቀፍ የመቀየር ለውጥ ነው።” በማለት የውይይቱን አስፈላጊነት አስገንዝበዋል። በመጀመሪያው ምእራፍ ለውይይት የቀረበውን ረቂቅ ሰነድ አስመልክተው ፕ/ር ፍቅሬ ሲናገሩ፡- “ለውይይት የቀረበው የተማሪዎች ምልመላ፣ መረጣና ቅበላ ረቂቅ የፖሊሲ ሰነድ፣ ለዩኒቨርሲቲው የራስ-ገዝነት ጉዞ አንድ ወሳኝና መሰረታዊ ጉዳይ ነው።” ብለዋል። ባለፉት ዓመታት የሪፎርም ዕቅድ በማዘጋጀት የተለያዩ ስራዎች እንደተሰሩ አስታውሰው፣ የቅበላ ፖሊሲው፣ ቀድሞ እንደነበረው ከሲቪል ሰርቪስ ተቋማት ተማሪዎችን በስኮላርሺፕ የመቀበሉ ሂደት እንዳለ ሆኖ፣ ከሲቪል ሰርቪስ ተቋማት ውጪ ያሉትን እና ከሀገር ውጪ የሚያመለክቱ ተማሪዎችን በክፍያ የምንቀበልበትን ህግና መስፈርት የሚይዝ ፖሊሲ መሆኑን ገልጸዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ዩኒቨርሲቲያችን በርካታ አካዳሚያዊ ነጻነቶችን



እንደሚቀዳጅ ገልጸው “ከእነዚህ አካዳሚያዊ ነጻነቶች መካከል አንዱ ተማሪዎችን በራሳችን መስፈርት መልምለንና መርጠን የመቀበል ነጻነት ነው፡፡” ሲሉ ተናግረዋል፡፡ በዶ/ር ተመስገን ቢረጋ የአካዳሚክ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አማካኝነት የቀረበው የመጀመሪያው ረቂቅ ሰነድ፡- “የኢሲሰዩ የተማሪዎች ምልመላ፣መረጣና ቅበላ ረቂቅ ፖሊሲ” የሚለው ሲሆን፣ በውስጡም የመጀመሪያ ዲግሪ፣ የሁለተኛ ዲግሪና የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን መመዝገብ፣ መምረጥ፣ መቀበል እና ማስተማር ድረስ ያለውን ሂደት መስፈርቶቹን ጨምሮ የያዘ ነው፡፡ እንዲሁም፣ የውጪ ሀገር አመልካቾች በዩኒቨርሲቲው ለመማር ማሟላት የሚያስፈልጓቸውን መስፈርቶችን አካቷል፡፡ ሁለተኛው “የኢሲሰዩ የትምህርት ጥራት ማስጠበቂያ ረቂቅ ፖሊሲ” በዶ/ር አሰፋ በየነ በአመራርና አስተዳደር ኮሌጅ የጥራትና ሥርዓተ-ትምህርት ጉዳዮች አስተባባሪ አማካኝነት የቀረበ ሲሆን፣ የትምህርት ጥራትን በተመለከተም ቀድሞ በዩኒቨርሲቲው ይሰራበት የነበረው የትምህርት ጥራት ፖሊሲ፣ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሲታይ ያለውን ክፍተት በመመርመርና ክፍተቱን ለመሙላት፣ የተለያዩ የሀገር ውስጥና በውጪ ሀገራት የሚገኙ ተቋማትን ተመክሮ በማገናዘብ፣ የተዘጋጀ ረቂቅ ፖሊሲ መሆኑ የተጠቀሰ ሲሆን፣ አስራ ሁለት የትኩረት መስኮችን በመለየት የተዘጋጀ ለመሆኑ በረቂቁ ተመላክቷል፡፡ ከእነዚህ የትኩረት መስኮች መካከልም የሥርዓተ-ትምህርት ቀረጻና ክለሳ፣ የሰራተኞች



ብቃትና ልማት፣ የተማሪዎች ግምገማና ምዘና፣ የተማሪዎች ድጋፍ አገልግሎት፣ መሰረተ ልማትና የመማሪያ ግብዐቶች፣ ቀጣይነት ያለው የጥራት ማሻሻያ፣ አለማቀፋዊነትና ትስስር፣ ሥነ-ምግባርና የአካዳሚያዊ ምሉዕ ሰብዕና፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፣ አካዳሚያዊ አመራርና



የፕሮግራም አስተዳደር እና ሌሎችም ጉዳዮችን ይዟል፡፡ ሶስተኛው “የኢሲሰዩ የስልጠና ጥራት ማስጠበቂያ ረቂቅ ፖሊሲ” በአቶ ብርሃኑ ንጉሴ የየስልጠና ኢኒስቲትዩት የስልጠና ጥራትና ሞጁል ጉዳዮች አስተባባሪ አማካኝነት የቀረበው ሲሆን፣ በዚህም ውስጥ ስልጠናው የሚመራባቸው እና ጥራቱን ሊያስጠብቁ የሚያስችሉ ዝርዝር ጉዳዮች፣ ማለትም፡- የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ማካሄድ፣ የስልጠና ካሪኩለም እና የፕሮገራም ቀረጻ፣ የስልጠና አሰጣጥ ሥርዓት፣ ስልጠናን የማስተባበር ሂደት እና የበጀት አመዳደብ ወዘተ. የመሳሰሉት ጉዳዮችን አካቶ የያዘ ነው፡፡ አራተኛው ረቂቅ፡- “የኢሲሰዩ የአካዳሚክ ሰራተኞች አፈጻጸም ምዘና ረቂቅ መመሪያ” የሚለው ሲሆን፣ አቅራቢው ዶ/ር አድማሱ ቴሶ የትምህርትና ስልጠና ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ናቸው፡፡ በረቂቅ ሰነዶቹ ላይ ከተሳታፊዎች በርካታ ገንቢ ሀሳቦች የተነሱ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል አመልካቾችን በዕድሜ የመገደብ ሁኔታ፣ የባንክ ሂሳብ እንዲቀርብ መጠየቅ፣ በአንድ ጊዜ ሁለት በተለያዩ የትምህርት ፕሮግራሞች መማርን በተመለከተ፣ ምዝገባንና ቅበላን በኦንላይን የማድረግ ሂደት፣ ተማሪዎችን የመለየት ሂደት የሚሉ እና ሌሎች በርካታ ሀሳቦች ተነስተው ተሳታፊዎቹ በስፋት ተወያይቶባቸዋል፡፡ በቀጣይ የቀረቡት በምርምርና ማማከር ዘርፍ ውስጥ የሚኖሩተግባራትንለመምራትሚያስችሉፖሊሲዎችደንቦች እናመመሪያዎችሲሆኑእነዚህንአስመልክተውየዩኒቨርስቲዉ ፕሬዚዳንት ፕ/ር ፍቅሬ ዳሳለኝ፣ የቀጣዮቹ ሰነዶች ትኩረት የዩኒቨርሲቲው ተልዕኮ ምሰሶ እና እስትራቴጂካዊ ዘርፍ በሆኑት በምርምርና ማማከር ላይ መሆኑን ገልጸው፣ “የምርምር እና የማማከር ሥራዎች የዩኒቨርሲቲያችንን

ህልውና የሚወስኑ በመሆናቸው እንደ አንድ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም መቀጠል ካለብን የምርምርና የማማከር ሥራን በጥራት እና በዓለም-ዓቀፋዊ ስታንዳርድ መሰራት አለብን፤ በምርምርና ማማከር ሥራ የቀጨጨ ዩኒቨርሲቲ፣



ዩኒቨርሲቲ ሊባል አይገባውም፤ ተፈላጊ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ሊሆንም አይችልም። ዩኒቨርሲቲ ከሌሎች ተቋማት የሚለየው፣ ጠንካራ የምርምር ውጤት ሲያፈልቅ ነው።" በማለት የውይይቱ ተሳታፊዎች በሚቀርቡት ሶስት ረቂቅ መመሪያዎች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ማሳሰቢያ ሰጥተዋል።

በማስከልም አምስተኛው "የኢሲሰዩ የምርምር አስተዳደር ረቂቅ መመሪያ" በዶ/ር ዘሪሁን ዶዳ የምርምር ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አማካኝነት ቀርቦ በርካታ እና ፋይዳ ያላቸው ሀሳቦች ተሰንዝረውበታል። ስድስተኛው "የኢሲሰዩ የምርምር በጀት ድጋፍ አስተዳደር ረቂቅ መመሪያ" በዶ/ር ሙከሪም ሚፍታህ የግራንት ማፈላለግና ትብብር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አማካኝነት ቀርቦ፣ ከፋይናንስ እና ከተመራማሪዎች ክፍያ ጋር የተገናኙ በርካታ ጥያቄዎች የተስተናገዱበት ሲሆን፣ ቢካተቱ መልካምነውየተባሉአስተያየቶችእናተመክሮዎችቀርበዋል። ሰባተኛው እና የመጨረሻው ረቂቅ ሰነድ "የኢሲሰዩ የተመራቂ ተማሪዎች ምርምር ማስተባበሪያና ድጋፍ ረቂቅ መመሪያ" የሚለው ሲሆን አቅራቢውም ዶ/ር ታረቀኝ ዲኣ የድረ ምረቃ ምርምር አስተባባሪ ናቸው። በዚህም ላይ የተማሪዎችን የምርምር ስራዎች ከመመሪቂያነት ባለፈ ለሀገራዊ ጥቅም ማዋል በሚቻልበት ስርዓት ላይ ውይይት ተካሂዶበት የየዘርፉ ምክትል ፕሬዘዳንቶች በረቂቅ ሰነዶቹ ላይ ለተነሱ ጥያቄዎችየሚመለከታቸውንምላሽእናማብራሪያሰጥተዋል። በመጨረሻም የዩኒቨርስቲዉ ፕሬዚዳንት ፕ/ር ፍቅሬ ዳሳለኝ፣ ራስ-ገዝነት ከሚያጎናጽፈው ነጻነት አንዱ ተቋማት በራሳቸው ጥራትንየሚያስጠብቁበትና የበለጠ ተወዳዳሪ ሊያደርጋቸው የሚያስችላቸውን የትምህርት ጥራት ማስጠበቂያ ስልት ሊከተሉ የሚችሉበት ነጻነት መሆኑን ገልጸው፣ "ጥራት ከኢሲሰዩ አንጻር ሲታይ ለታለመለት ዓላማ የሚውል፣ ብቁና ተወዳዳሪ የሆነ፣ የተሰጠውን ተልዕኮ በብቃት የሚወጣ የሰው ኃይልን ማፍራት ማለት ነው።" ብለዋል። አስከትለውም የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት፣ አስፈላጊ የሆኑ ግብዐቶች፣ የትግበራ ሂደትና የሚጠበቀው ውጤት የሚሉት ነጥቦች ላይ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተዋል፤ ለትምህርት ጥራት እንደ ግብዐት ከሚያስፈልጉ ወሳኝ ጉዳዮች መካከል ተገቢ የሆነ ተማሪ፣ የትምህርት ስርኣት፣ በቂ ቁጥርና ብቃት ያለው መምህር፣ በቂ መሰረተ-ልማት፣ የአሰራር መመሪያዎችና ደንቦች እና ሌሎችንም ለአብነት ጠቅሰዋል። ፕ/ር ፍቅሬ ለውይይት ቀርበው ሃሳብ የተሰጠባቸው ረቂቅ ሰነዶች ጸድቀው ወደ ትግበራ ሲገቡ ለዩኒቨርሲቲው የሚያስገኙለት አካዳሚያዊ ነጻነቶች ደረጃ በደረጃ ሲያስቀምጡ፦ "እነዚህ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች፣ ዩኒቨርሲቲው የራሱ የሆነ የትምህርት ጥራት ማስጠበቂያና አዋጭና ተመራጭ የሆኑ የትምህርት ፕሮግራሞችን መቅረጽ እና ማስጀመር የሚያስችሉ ናቸው። የረቂቆቹ ዋና ትኩረት የውስጥ ጥራትን ማስጠበቅ ነው። እነዚህ ከመጀመሪያ ጀምሮ ያየናቸው ዩኒቨርሲቲው በራስ-ገዝነቱ ሂደት በመጀመሪያው ምእራፍ የሚጎናጸፋቸው ነጻነቶች ናቸው፡



፡" ካሉ በኋላ በሁለተኛው ዙር ደግሞ ሀብት የማፍራት፣ በራስ ገቢ የመንቀሳቀስ የፋይናንስ ነጻነት፣ ብቃት ያለው ስታፍ የማደራጀት እና መዋቅራዊ ነጻነቶች እንደ ተቋም ዩኒቨርሲቲው የሚጎናጸፋቸው ነጻቶች እንደሚሆኑ ገልጸው፣ ሀብትን የመፍጠርና የማንቀሳቀስ አቅም ማግኘት፣ የተሻለ

ጥራት ያለውና ተወዳደሪ የትምህርት ተቋም የመሆን ዓላማን ለማሳካት የሚያስችል የለውጥ እሳቤ እንደሆነ አስገንዝበዋል። ፕ/ር ፍቅሬ የትግበራንም ሂደት አስመልክተው ሲናገሩ ጠንካራ የትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት፣ ጠንካራ የሆነ የምዘና ሥርዓት፣ ጠንካራ የሆነ የውጤት አሰጣት፣ የምሩቃንን ብቃት ማረጋገጫ፣ የአስተዳደርና አካዳሚየዊ ድጋፍ ስርዓት መኖርን ከዘረዘሩ በኋላ፣ "የዚህ ሁሉ መጨረሻና ተጠባቂው ውጤት፣ ብቁና የተሰጠውን ተልዕኮ መወጣት የሚችል ምሩቅ ማፍራት ነው።" ብለዋል። የዚህ ሂደት ግብ በዩኒቨርሲቲው ራስ-ገዝነትን ማስፈን መሆኑን አውስተው፣ ራስ-ገዝነትም ለትምህርት ተቋማት አካዳሚያዊ ነጻነትን ከመስጠቱም ባሻገር፣ እራሳቸውን



በተሻለ እንዲያስተዳድሩ ከቀድሞው ከፍ ያለ፣ በህግ የተቀመጠ ነጻነትን እንደሚያስገኝላቸው አብራርተዋል። ሲያጠቃልሉም በርካታ ጥሩ የሆኑ ሀሳቦች ከቤቱ መነሳታቸውን



እና ሰነዶቹም ጊዜ ተወስዶና የተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጪ ተቋማትን ተመክሮዎች በማካተት የተዘጋጁ መሆናቸውን አድንቀው፣ የተነሱትን ሀሳቦች እንደግብዐት እንደሚወስዱ እና አስተያየቶቹን በማካተት የቀረቡት ረቂቅ ፖሊሲዎች የበለጠ የሚዳብሩ መሆናቸውን ገልጸው ወርክሾፑን አጠቃለዋል።



# የዓለም አቀፍ የኤች አይ ቪ/ኤድስ፣ የአካል ጉዳተኞች እና ጾታዊ ጥቃትን የመከላከል ቀን በኢሲሰዩ ተከበረ

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የዓለም አቀፍ የኤች አይ ቪ/ኤድስ፣ የአካ ጉዳተኞች እና ጾታዊ ጥቃትን የመከላከል ቀንን ታህሳስ 10 ቀን 2017 ዓ.ም በኤች አይ ቪ/ኤድስ፣ የአካል ጉዳተኝነት እና ጾታዊ ጥቃት ዙርያ ውይይት በማድረግ ተከበረ፡፡

በውይይት መድረኩ ላይም አቶ ዝናቤ ታደሰ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች አካቶ ትግበራ ሥራ አስፈጻሚ ባደረጉት



የመክፈቻ ንግግር በተለያዩ ተቋማት ጾታዊ ትንኮሳዎች እየተስተዋሉ መሆናቸውን ገልጸው ይህን ጥቃትና ትንኮሳ ለማስቆምም ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በያገባኛል መንፈስ ሊንቀሳቀስ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡ የአካል ጉዳትን በተመለከተም ከህንጻዎች ምቹ አለመሆን ባሻገር የሚሰጠውም ትምህርት የአካል ጉዳት አካታችነት ላይ ክፍተት የሚስተዋልበት በመሆኑ አካል ጉዳተኝነትን አካቶ መስራት ተገቢ መሆኑን እንዲሁም የኤች አይ ቪ ኤድስ ስርጭትም አሁን ላይ ችላ በመባሉ ምክንያት እንደገና እያገረሸ በመሆኑ እንደ ማህበረሰብ በስፋት መስራት አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በአጠቃላይም እነዚህን ችግሮች ለማስቀረትና ምቹ የሆነ አካባቢ እንዲኖር ሁሉም የስራ ክፍሎች የየራሳቸውን ድርሻና ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡም አቶ ዝናቤ አሳስበዋል፡፡ በእለቱም "ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት" እና "በአዲስ አበባ ባሉ ከፍተኛ የመንግስት የትምህርት ተቋማት ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ያሉ ምቹ ሁኔታዎችና የሚያጋጥማቸው ተግዳሮቶች" የሚሉ ሁለት የመወያያ ሰነዶች በዶ/ር አዜብ አሰፋ እንዲሁም በዶ/ር አባይ አክማቸው እና በአቶ ኪዳነማርያም ግደይ የቀረቡ ሲሆን በቀረቡት ሰነዶች ላይም ተሳታፊዎች ዉይይት አድርገዋል፡፡ በቀረቡት የመወያያ ሰነዶችም ስርዓተ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚፈጸም አካላዊ፣ ወሲባዊ፣ ሥነ- ልቦናዊ እና ኢኮኖሚያዊ የሰብዐዊ መብት ጥሰት መሆኑ እና አካላዊ ፣ ስነ ልቦናዊ፣ ወሲባዊ እና ኢኮኖሚያዊ መልኮች እንዳሉት፣



ጥቃቱም ዓለማቀፋዊ እንደሆነ እና በአፍሪካም በከፍተኛ ደረጃ እየታየ መሆኑም ተጠቅሷል፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍም የማህበረሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፣ የህግ ማዕቀፎችን ማዘመንና በአግባቡ መተግበር፣ ለተጠቂዎች የህግ ከለላ መስጠትና መንከባከብ እንዲሁም ሌሎች ስትራቴጂዎችን መጠቀም አስፈላጊ መሆኑ ተመላክቷል፡፡ የአካል ጉዳትን በተመለከተም የአካል ጉዳተኞች በመማር ማስተማሩ ሂደት በርካታ ችግሮች እንደሚያጋጥሟቸው በጥናቱ የተገለጸ ሲሆን የመሰረተ ልማቶች ምቹ አለመሆን፣ ከአመለካከት ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶች፣ በአካዳሚኩ ላይም የአካታችነት ችግር መኖር እና ሌሎችም ችግሮች መኖራቸው ተጠቅሷል፡፡ ለዚህም መሰረተ ልማቶችን ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ማድረግ፣ አስገዳጅ የሆኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፣ ስርዓተ ትምህርቶችን አካታች ማድረግ፣ የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎትን ማጠናከር፣ አጋዥ ቴክኖሎጂዎችን በበቂ ሁኔታ ማቅረብና ሌሎች የመፍትሔ ሀሳቦች ቀርበው በተሳታፊዎች ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡



# ECSU held a Conference on Migratory Trends in the Horn of Africa

Ethiopian Civil Service University (ECSU) College of Leadership and Governance, Institute of African Governance and Development held a Conference on Migratory Trends in the Horn of Africa on October 23, 2024 at ECSU.

Dr. Melkamu Moshago Department Head of Institute of African Governance and Development at ECSU , warmly welcomed all honorable guests, Ambassadors, academic staffs ,invited guests and students. He highlighted the benefit of organizing such kind of academic conferences and sharing experiences among the academician. He also presented the academic and work experience of the speakers.



*Alemayehu Debebe (PhD),*
*Vice President for Research and Partnership*



*Lemma Gudissa Angessa (PhD),*
*Vice President for AcademicAffairs,*

Lemma Gudissa Angessa (PhD), ECSU Vice President for Academic Affairs, welcomed the participants and briefed the overall establishment of the university and its achievement for the last three decades and briefed the academic wing profile and academic programs of ECSU.

He also noted that the issue of Migration is very sensitive especially in the horn of Africa because of different reasons. As he explained primary drivers of the common migrations reasons are limited economic opportunity, conflict, growing youth populations, and climate change. So that handling such issues sci-





entifically and creating expert in this area is vital and ECSU is on the way to open graduate program in the area for the coming academic year he underlined. H.E. Attila Tamás Koppány, Ambassador of Hungary to



Ethiopia, in his presentation mentioned some Migratory challenges that faces the world and also human suffering in Africa is increasing. Identifying the root cause of migration and finding a better solution by engaging the community, educating the youth and localization of the issue are vital, he proposed.

The first speaker, Prof Dr. Istvan Tarrossy, from University of Pecs, briefly States the causes of Migration such as search out for land and employment. Positive and negative approaches are implemented to understand the major focal point of Migration



as new tendencies are seen like many young Africans go to Asia; in the opposite , two million Chinese are living in Africa nowadays compared to 150,000 Chinese were in 2014 he added. So that making regional efforts, securitization of Migration, intercontinental solidarity and cooperation, short and reactive solutions are the main solutions to minimize the tendencies of Migration he concluded.



Dr.Victor Marasia, from Ludovika University of Public Service, in his part identified countries that highly affected by displacement in the past years. Ethiopia, Sudan, and Uganda hosts the highest number of refugees in the Horn of Africa and the number of migrants increased four times from 750,000 to 2.5 million. The case study on Sudan showed that the result of civil war increased the



number of migrants he underlined. Dr. Judit Kiss, from International Business School and Budapest Institute of world Economics, proved the positive side of Migration. As she explained that gaining a large amount of remittance for a better economic development for Africa countries should be seen recently as an advantage for the economy of the continent. Although most researches do not show the positive side of Migration, Africa gains 4 billion dollar from remittance. So we better convert illegal sources to legal sources and make solid base of economic growth and advocate the macro and micro impacts of Migration, she summarizes. Dr. Szabolch Pasztor,from Ludovika University of Public Service, described 25% of the global working age is found sub-Sahara countries and among this 191 million people lives in Ethiopia, Sudan, South Sudan, Djibouti, and Eretria. He also pointed out the relationship and consequence between economic growth and population growth.



H.E Dr. Ramiz Alakbarov,from UN Resident and Humanitarian Coordination in Ethiopia, remarked and briefed the advantage of thinking globally is the issue of Migration for further solution in the world.



Dr. Tsega Gebrekerestos and Dr. Mohamed Ali, from Ethiopian Civil Service University, explained the impact and vulnerability of migration on the society, respectively. Dr. Tsega pointed out whether migration is an opportunity or a treat to Ethiopia. According to the UN data, from the total number of population Ethiopian, only 23% lives in urban areas. So that the migration of people from rural to urban increases because of drought, shortage of farm land, lack of jobs, low wages, debt and conflict. Dr. Mohamed Ali in his part clarified the vulnerable group of the society such as women, children and disable people that are highly affected by civil war, drought and displacement. He also explained that why developed countries should not consider migration as a global issues.

The Conference on Migratory Trends in the Horn of Africa is prepared by ECSU Institute of African Governance and Development and Embassy of Hungary in Ethiopia.

# ECSU President and NSG Principal Holds Meeting on Bilateral Cooperation

Professor Fikre Dessalegne, Ethiopian Civil Service University President, and Prof. Busani Ngcaweni, National School of Governance Principal, Republic of South Africa, discussed on the bilateral cooperation between the institutions on December 11, 20024 at Senate Hall of the University.



Professor Fikre Dessalegne welcomed the team lead by Prof. Busani Ngcaweni and introduced the overall academic programs, journals, academic staff profile, the research outputs and campus of ECSU in brief .He also explained Ethiopian Civil Service University special mission of building the capacity of the civil servants by providing education, short term training, research and consultancy service. Partnership is one of the platform for ECSU for sharing experience, knowledge and resources. So we are very happy to work together and share experiences by making strategic collaboration and establishing a framework of cooperation between the two institutions. NSG and ECSU will achieve mutually beneficial goals in several common interest through the bilateral cooperation he added. Prof. Busani Ngcaweni thanked ECSU management for welcoming his team and explained in briefed about the National School of Governance history and establishment. Partnership which is working together with partners internationally and nationally is one of the NSG objective. So we are ready to make this dissuasion fruitful and bring remarkable results .Besides, we are confident that this partnership will yield remarkable outcome and contribute significantly to the academic and cultural exchange between the two institutions he emphasized.





The NSG has a mandate to deliver quality education, training and development interventions that are relevant to the needs of the public sectors with the Mission of Empowering Public Servants to be Responsive to Citizen Needs and Government Priorities, through Education, Training and Development interventions.

# An Online Event Holds at ECSU

A webinar Training hosted by Ethiopian Civil Service University, College of Leadership , Department of Development Communication and Media Studies in Collaboration with South Korea' Peace Education Center under the theme "Let us bury ourselves in peace, and become a source of peace" on 4 December 2024 at Hidasse Hall.



The training was organized through online ZOOM meetings, and involves university community to create awareness about how to create strong bondage among individuals with diverse backgrounds, including different races, religions, cultures, ideologies, and appearances and come together to form harmonious relationships. Dr. Waqgari Negari , Head of Department of Development Communication and Media Studies, stated that the program aims to train students and university community in peace education and add the values of peace in individuals and cultivate peaceful citizens having qualities of gratitude ,consideration, sacrifice, forgiveness, and respect based on love. Peace is the greatest legacy we can leave to the future generations and contribute the development of society he added. HWPL peace education vision and goal aims for the heroes responsible for the next generation to become citizens of peace, cultivate the spirit of peace, and solve global security problems so that they become leaders who create global harmony and achieve peace.

## ECSU Gives Orientation for New Entry Students

Ethiopian Civil Service University (ECSU) Registrar Office gave orientation for students who joined the university for the academic year 2024/25 at Hidasse Hall on December 16, 2024.

Lemma Gudissa (PhD), ECSU Vice President for Academic Affairs, welcomed the new entry students and explained the overall history of ECSU and explained what are expected from the students and the university based on ECSU legislation. He also wished a successful learning time to all students and advised them properly utilize the opportunity and their time. Dr. Daniel Lirebo, ECSU Main Registrar, highlighted the overall information about ECSU and explained students' responsibilities and rights while they stay at ECSU. Besides, Colleges and School Deans and Vice Deans briefly explained their respective colleges and schools programs, facilities, staff profiles and the supports which is given for female and disable students. Dr. Workenehe Eshetu , Library and Documentation Directorate, briefed what behavior expected from library users and detail explanation of ECSU library services. Ato Zinabe Tadesse, Gender and H IV AIDS Issues Executive, quoted the proclamation number 624 and the general infrastructure of the university. He also emphasized that any Violence against women is intolerable in the university compound .Besides he explained services and supports that his office facilitates.





# ECSU President Discusses with Cultural Affairs Officer at the US Embassy

President of Ethiopian Civil Service University, Professor Fikre Dessalegne, discussed with Ryan Bradeen, Cultural Affairs Officer at the US Embassy in Addis Ababa, on potential partnership opportunities between the parties on November 2, 2024 at ECSU Senate Hall.



Professor Fikre welcomed the USA cultural affairs team lead by Ryan Bradeen and explained the overall Ethiopian Civil Service University establishment and its journey in the last three decades. Besides, he briefed what the university has done for the last two years in different phases to be an autonomous university and what will be done in the coming three consecutive years .He also briefed ECSU interest to create strong relations and make strategic partnership on different areas with international partners. Dr. Abrham Hagos, ECSU President's Office Head, in is part explained the university's overall profile and its strategic goal as research and autonomous university and its achievements to the team. Mr. Ryan Bradeen also explained USA and Ethiopian long relations in different areas and Education sector .He also expressed his interest to make collaborations and work together with Ethiopian Civil Service University in different academic areas. The discussion also focused on how to make different potential partnership and collaboration including workshop and seminar, joint research in different thematic areas, training and staff development,





# ECSU Holds a seminar on Necessity of Tax Reform for Ethiopia

Ethiopian Civil Service University College of Finance, Management and Development, Department of Tax and Customs Administration held a seminar entitled "Necessity of Tax Reform for Ethiopia", on December 20, 2024 at Hidasse Hall.

At the opening of the program, Lemma Gudissa (PhD), ECSU Vice President for Academic Affairs, welcomed the participants and the presenters .He also recap the historical background of ECSU. He thanked the program organizer and the presenters who are e willing to share their invaluable experience to the university community and invited guests. Prof. Dr. V. kommer, Executive Board Member and Director of Tax and Governance Consultancy Service, IBFD, thanked for the warm welcome. He also explained the current status of tax at the international arena in different countries. Tax has a significant progress in Creating and improving governance that need to ensure




the growth in equitable way across the society. He also highlighted the issues of inflations, and the advantage of taxpayers. Tax authority must be an integral part of budget formulating, planning and control he added. Professor Dr. Fesehatsion Menghistu, Tax and governance advisor, revealed that tax incentives alone are not the most important instrument of attraction of a foreign direct investment. Investors in developing countries are given license without being strongly scrutinized by government body. He emphasized that in the name of free market the poor are getting poorer and the rich are getting richer. FDI is still one of the most sensational, complex as well as ideological controversial devise not only with in government policy makers and political but also with in the academicians, he summarized.



Participant from University community, Ministry of



Finance, and Ministry of Revenue raised different questions and suggestions and the presenters responded for the questions raised by the participants. At the end, Certificate of appreciation is given for the presenters.



# International Bureau of Fiscal Documentation Delegates Visits ECSU

Visiting scholars from International Bureau of Fiscal Documentation (IBFD) paid an educational visit to Ethiopian Civil Service University on December 17, 2024.





IBFD delegates were welcomed by ECSU President, Professor Fikre Dessalegn, and discussed on the strengthening of their partnership and collaboration between IBFD and Ethiopian Civil Service University. The President explained ECSU success since its establishment and the importance of academic alliance with different International and local institutions. ECSU is working with different international and local institutions in different areas by establishing academic collaborations and partnerships. It also shares its ambitions, values and aspirations he added.

Dr.Abreham Hagose, Head of President Office, highlighted about ECSU establishment and achievements registered in the last three decades in the area of education, training, research, and partnership. He also briefed a ten year strategic plan and the focus area of the University in the coming three years especially in the area of internationalization and partnership. Dr.Abreham also noted that ECSU has produced more than fifty thousand graduates serving in the public service sectors of the country in different hierarchies including Ministers. Besides, the University has been providing scholarship programs to the neighboring countries and more than 448 public servants have completed their first and second degree he emphasized.






Professor Dr. Victor van Kommer, Member of the Executive Board and Director of the National and International Tax Service of the IFBD also briefed about IBFD and explained that the establishment of IFBD opens a door for international tax knowledge throughout the world especially topics related to tax policy, transfer pricing, group taxation, indirect taxation, international taxation and tailored to government.

# ECSU Holds a Seminar on different programs and Opportunities provided for scholars by US Government

The U.S. Embassy in Addis Ababa, in collaboration with Ethiopian Civil Service University, School of Law held a Seminar on different programs provided by US Government for scholars and Academicians on November 2, 2024 at ECSU Hidasse Hall.

Ryan Bradeen, Cultural Affairs Officer at US Embassy in Addis Ababa, emphasized the US cooperation with Ethiopia, especially in the educational and cultural exchanges. He also overviewed the different programs including the Fulbright Program, the Humphrey Fellowship program, the International Visitors Leadership Program (IVLP), and the Mandela Washington Fellowship for Young African Leaders to the University Community. Ms. Eyerusalem Mandefro,Cultural Affairs Assistant at the US Embassy in Addis Ababa ,explained what the Fulbright Program, the flagship international academic exchange program provides op-





portunity for students, scholars, teachers, artist and professionals in each year and what the Humphrey Fellowship Program provides to young and mid-career professionals an opportunity to enhance their professional capacities through participation in specialized 10-month non degree programs developed specifically for selected U.S. universities. Ms.Wubakal Beyene Public Engagement Assistant at the US Embassy in Addis Ababa, also explained the Young African Leaders Initiative (YALI) program to bring African civic, business, and community leaders for academic coursework, leadership training, and networking at U.S. colleges and universities. Mr.Teklemichael Tefera, American Spaces Director and Education USA Advisor at U.S embassy in Addis Ababa, notes about Graduate Program study in the United State and the overall higher education system in USA. At last the participants raised different questions and comments for presenters concerning to the different programs offered by the US government.





# SGS Organizes PhD Dissertation Defense Programs

Ethiopian Civil Service University School of Graduate Studies organized PhD defense programs from December 3-4, 2024 at ECSU.

Amsalu Bedemo, Assoc. Prof., Director of School of Graduate Studies, has commended the successful defense of PhD dissertation, held on 3-4 November 2024, at the main campus of Ethiopian Civil Service University. He also emphasized the university's commitment to growth and excellence, particularly in postgraduate education and highlighted that ECSU continues to expand its range of programs across its Colleges and Schools to diverse academic and professional need.

On the program, the candidates, presented their PhD dissertation papers in different areas at the presence of the Board of Examiners which included the internal and external examiners and they defended for the questions forwarded by the examiners. As the result of the defense the Examination Board for doctoral dissertation defense announced that candidates have been awarded PhD degree.



Ethiopian Civil Service University
Committed to Excellence in the Public Sector

Contact Address:
Hot line: +251-116-46-30-15
Tel.0116 46 2887
Fax: 0116463016
P.O.Box5648
E-mail: IPRD@ecsu.edu.et
Pr.ecsu@gmail.com
Website: www.ecsu.edu.et
Tweeter: @ECSU tweets
FM Radio:-100.5MHz
Facebook: Ethiopian Civil Service University